**የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ**

# የምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመሮች መጠበቅ ስለሚገባቸው ርቀቶችና የአቅርቦት ጥራት መመሪያ

**አዲስ አበባ**
***1998***


**የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ**

***ፖስታ ሣ.ቁጥር 2554***
**ስልክ 011-550-77-35/52/54**
**ፋክስ 011-550-77-34**
**ኢ-ሜይል e.agency@ethionet.et**
**አዲስ አበባ**

## *የኤሌክትሪክ መሥመሮችና የአቅርቦት ጥራት መመሪያ ቁጥር ኢ.ኤ.ኤ./1/2005*

## *ምዕራፍ አንድ*

## *ጠቅላላ*

**1 *አውጭው ባለሥልጣን***

*የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ በኤሌክትሪክ ሥራዎች የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 49/1991 በአንቀፅ ቁጥሮች 55፣ 67 እና 69 በተሠጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡*

**2 *አጭር ርዕስ***

*ይህ መመሪያ "የኤሌክትሪክ መሥመሮችና የአቅርቦት ጥራት መመሪያ ቁጥር ኢ.ኤ.ኤ./1/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡*

**3 *ትርጓሜ***

*የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም እንዲሠጠው ካላደረገ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ ያሉ ቃላት በኤሌክትሪክ አዋጅ ቁጥር 86/1989፣ በኤሌክትሪክ ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 49/1991 እና እነዚህኑ ለማስፈፀም በወጡ መመሪያዎች ውስጥ ያላቸው ትርጉም የተጠበቀ ሲሆን በዚህ መመሪያ ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ ሌሎች ትርጓሜዎች፣*

3.1 *"መሣሪያ" ማለት ማናቸውም የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት፣ ለማስተላለፍና ለማከፋፈል የሚያገለግል ተቋም፣ መሣሪያ ወይም መገልገያ ሲሆን እንዲሁም ለኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚዎች ለመብራት፣ ለማሞቂያ፣ ለተንቀሣቃሽ ኃይልና ለሌሎች አገልግሎቶች እንዲውሉ የታቀዱ የኤሌክትሪክ መስመሮች፣ ተገጣሚ እቃዎችና መገልገያዎችንም ይጨምራል፡፡*

3.2 *"የኤሌክትሪክ መስመር" ማለት የኤሌክትሪክ ኃይልን ለማስተላለፍ ወይም ለማከፋፈል የሚያገለግል ሽቦ ፣ ኤሌክትሪክ አስተላላፊ ገመድ ወይም ሌላ ነገር ሲሆን መስመሩን ወይም ማናቸውም የመስመሩን ክፍል የሚሸፍን ወይም የሚደግፍ ማንኛውንም ጠንካራ ልባስ፣ ቅብ፣ ሽፋን፣ ቱቦ፣ ቧንቧ ወይም አቃፊ የሆነ ማናቸውንም ነገር ይጨምራል፡፡ "*

3.3 *"ሽፍን ሽቦ" ማለት በአይነቱና በውፍረቱ በቂ የኤሌክትሪክ ኢንሱሌሽን በሚሰጥ ንጥረነገር የተሸፈነ ሽቦ ነው፡፡*

3.4 *"ሽፋን" ማለት አስተላላፊ ካልሆነ ነገር የተሠራ አስተላላፊ ሽቦን ወይም ማናቸውም የሽቦውን ክፍል አቅፎ፣ ከልሎ ወይም ደግፎ የሚይዝ ነገር ሲሆን ቃሉ ጥቅም ላይ በዋለበት አንቀጽ ውስጥ ለተጠቀሰው አገልግሎት የሚመጥን ተገቢ ጥራትና ውፍረት ያለው ነው፡፡*

3.5 *"ሺ.ቮ." ማለት 1000 ቮልት ነው፡፡*

3.6 *"የምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመር" ማለት ከመሬት በላይ ክፍት በሆነ ቦታ የተዘረጋ ማንኛውም የኤሌክትሪክ መስመር ማለት ነው፡፡*

3.7 *"ተሸካሚ" ማለት የኤሌክትሪክ መስመሮችን ወይም መሣሪያዎችን የሚሸከም ማንኛውም ምሰሶ ወይም ደጋፊ አካል ሲሆ ኢንሱሌተሮችን፣ ተገጣሚዎቻቸውን ወይም ማንኛውንም ዋና ተግባሩ የኤሌክትሪክ መስመሮችን ወይም መሣሪያዎችን መደገፍ ያልሆነ ህንጻም ሆነ ግንባታን አያካትትም፡፡*

**4 *የመመሪያው ዓላማ***

*የዚህ መመሪያ ዓላማ በሰው ላይ አደጋ እንዲሁም በንብረት ላይ ጥፋት እንዳይደርስ ለመከላከል ለማስቻል ሲባል ከኤሌክትሪክ ማስተላለፍና ማከፋፈል መስመሮች ጋር በተያያዘ መጠበቅ ስለሚገባቸው ርቀቶች ደረጃ ለመወሰንና የአቅርቦት ቮልቴጅንም ጥራት ለመወሰን ነው፡፡*

## *ምዕራፍ ሁለት*

## *ከምድር በላይ የሚዘረጉ የኤሌክትሪክ መስመሮች እና የአቅርቦት ጥራት*

**5 *ከምድር በላይ የኤሌክትክ መስመሮችን ለመዘርጋት ገደቦችን ስለማድረግ***

*ማናቸውም ባለፈቃድ በማመንጫ ጣቢያዎችና በማከፋፈያ ጣቢያዎች ውስጥ ከሚኖሩት በስተቀር ከዚህ የመመሪያ ክፍል ጋር የማይጣጣሙ የኤሌክትሪክ መስመሮችን፣ ሽቦዎችን፣ ኬብሎችን ወይም ተሸካሚዎችን መጠቀም የለበትም፡፡*

## 6 *ከምድር በላይ የኤሌክትክ መስመሮች መጠበቅ ስለሚገባቸው ርቀቶች*

6.1 **የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6.2) እንደተጠበቀ ሆኖ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን እንደየሚመለከተው የመስመሩ ቮልቴጅ መጠን አንድ የምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመር ከምድር በላይ የሚኖረው ከፍታ ቀጥሎ ከተገለጹት ዝቅተኛ ርቀቶች ማነስ የለበትም፡፡**

6.1.1 **የመስመሩ ቮልቴጅ ከ1ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ መኪና በሚተላለፍበት መንገድ ላይ 5.5 ሜትር እንዲሁም በማናቸውም ሌላ ቦታ ላይ 4.6 ሜትር**

6.1.2 **የመስመሩ ቮልቴጅ ከ1ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ33ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ መኪና በሚተላለፍበት መንገድ ላይ 6.7 ሜትር እንዲሁም በማናቸውም ሌላ ቦታ ላይ 5.2 ሜትር**

6.1.3 **የመስመሩ ቮልቴጅ ከ33ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ66ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ መኪና በሚተላለፍበት መንገድ ላይ 8.0 ሜትር እንዲሁም በማናቸውም ሌላ ቦታ ላይ 6.5 ሜትር**

6.1.4 **የመስመሩ ቮልቴጅ ከ66ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ132ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ መኪና በሚተላለፍበት መንገድ ላይ 8.0 ሜትር እንዲሁም በማናቸውም ሌላ ቦታ ላይ 7.0 ሜትር**

6.1.5 **የመስመሩ ቮልቴጅ ከ132ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ230ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ መኪና በሚተላለፍበት መንገድ ላይ 10.5 ሜትር እንዲሁም በማናቸውም ሌላ ቦታ ላይ 8.0 ሜትር**

6.1.6 **የመስመሩ ቮልቴጅ ከ230ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ400ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ መኪና በሚተላለፍበት መንገድ ላይ 12.0 ሜትር እንዲሁም በማናቸውም ሌላ ቦታ ላይ 10.0 ሜትር**

6.2 **በማናቸውም የምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመር መኪና ከሚተላለፍበት መንገድ በላይ ባልሆነበት ቦታና ከሚከተሉት ውስጥ አንዱ ተፈጻሚ በሆነበት ሁኔታ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ተግባራዊ አይሆኑም፡፡**

6.2.1 **መስመሩ ሽፍን ከሆነ፣ ወይም**

6.2.2 **መስመሩ ሽፍን ሳይሆን ነገር ግን ቢያንስ ከምድር በላይ ከፍታው 4.3 ከሆነና በተጨማሪም ከማናቸውም የምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመር ተሸከሚ ላይ የተሰቀለ መሣሪያን የሚያገናኝ ከሆነ፣ ወይም**

6.2.3 **ከመሬት ጋር የተገናኘ ከሆነ.**

6.3 **በማንኛውም ጊዜ ቢሆን የዝቅተኛ ቮልቴጅ ሽፍን ሽቦ ካልሆነ በስተቀር አንድ የምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመር በህንጻዎች የፊት ለፊት ገጽ ላይ መያያዝ የለበትም፡፡**

6.4 **በማንኛውም ጊዜ ቢሆን አንድ የዝቅተኛ ቮልት ሽፍን ሽቦ ቀጥሎ ከተገለጹት ዝቅተኛ ርቀቶች የበለጠ ወደ ህንጻ ወይም ግንባታ አካላት መቅረብ የለበትም፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| 6.4.1 | **ከመሬት በላይ በቀጥታ** | **2.5 ሜትር** |
| 6.4.2 | **ከመስኮቶችና በሮች በላይ** | **0.3 ሜትር** |
| 6.4.3 | **ከመስኮቶች በስተጎንና በታች** | **0.5 ሜትር** |
| 6.4.4 | **ከበሮችና ባልኮኒዎች በስተጎን** | **1.0 ሜትር** |
| 6.4.5 | **ከህንጻዎችና ግንባታዎች ብረታማ አካላት** | **0.05 ሜትር** |

6.5 **በማንኛውም ጊዜ ቢሆን እንደየሚመለከተው የመስመሩ ቮልቴጅ መጠን አንድ የምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመር ቀጥሎ ከተገለጹት ዝቅተኛ ርቀቶች የበለጠ ወደ ህንጻ ወይም ግንባታ አካላት መቅረብ የለበትም፡፡**

6.5.1 **ሰው በተለምዶ ከሚደርስባቸው የህንጻ ወይም የግንባታ አካላት ቀጥታ ወደላይ ባለው አቅጣጫ በሚሆንበት ጊዜ የመስመሩ ቮልቴጅ ከ1ሺ.ቮ. ካልበለጠ 3.7 ሜትር እንዲሁም የመስመሩ ቮልቴጅ ከ1ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ33ሺ.ቮ. ካልበለጠ 4.6 ሜትር**

6.5.2 **ሰው በተለምዶ ከማይደርስባቸው የህንጻ ወይም የግንባታ አካላት ቀጥታ ወደላይ ባለው አቅጣጫ በሚሆንበት ጊዜ የመስመሩ ቮልቴጅ ከ1ሺ.ቮ. ካልበለጠ 2.7**

**ሜትር እንዲሁም የመስመሩ ቮልቴጅ ከ1ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ33ሺ.ቮ. ካልበለጠ 3.7 ሜትር**

6.5.3 **ሰው በተለምዶ ከማይደርስባቸው የህንጻ ወይም የግንባታ አካላት በማንኛውም ሌላ አቅጣጫ በሚሆንበት ጊዜ የመስመሩ ቮልቴጅ ከ1ሺ.ቮ. ካልበለጠ 0.6 ሜትር እንዲሁም የመስመሩ ቮልቴጅ ከ1ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ33ሺ.ቮ. ካልበለጠ 2.7 ሜትር**

6.5.4 **ከመስኮቶች፣ ክፍተቶች እና ባልኮኒች እንሁም ሰው በተለምዶ ከሚደርስባቸው የህንጻ ወይም የግንባታ አካላት በማንኛውም ሌላ አቅጣጫ በሚሆንበት ጊዜ የመስመሩ ቮልቴጅ ከ1ሺ.ቮ. ካልበለጠ 1.5 ሜትር እንዲሁም የመስመሩ ቮልቴጅ ከ1ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ33ሺ.ቮ. ካልበለጠ 2.7 ሜትር**

6.5.5 **ከእግር ድልድይ በማንኛውም አቅጣጫ በሚሆንበት ጊዜ የመስመሩ ቮልቴጅ ከ33ሺ.ቮ. ካልበለጠ 4.6 ሜትር**

6.6 **የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6.5) ድንጋጌዎች የምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመሩ ከምሰሶ ወይም ታወር ጋር የሚኖረውን መገናኘት በተመለከተ ወይም የኤሌክትሪክ ኃይል ለአንድ ህንጻ ወይም ግንባታ ለማቅረብ ሲባል ወደ ህንጻው ወይም ግንባታው በተጠጋው የምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመሩ ክፍል ላይ ተግባራዊ አይሆኑም፡፡**

6.7 **በማንኛውም ጊዜ ቢሆን እንደየሚመለከተው የመስመሩ ቮልቴጅ መጠን አንድ የምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመር አነስተኛ ስፋት ወዳለው የባቡር ወይም ትራምዌይ ሀዲድ ቀጥሎ ከተገለጹት ዝቅተኛ ርቀቶች የበለጠ መቅረብ የለበትም፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| 6.7.1 | **ከ1ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ** | **7.0 ሜትር** |
| 6.7.2 | **ከ1ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ66ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ** | **8.5 ሜትር** |
| 6.7.3 | **ከ66ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ230ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ** | **10.5 ሜትር** |
| 6.7.4 | **ከ230ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ400ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ** | **12.0 ሜትር** |

## 7 ከተክሎች መጠበቅ ስለሚገባው

7.1 **ከምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመሮች ስር ዛፎችን ማሳደግ የተከለከለ ነው፡፡ በማንኛውም ጊዜ ቢሆን እንደየሚመለከተው የመስመሩ ቮልቴጅ መጠን አንድ የምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመር በማናቸውም አቅጣጫ ቀጥሎ ከተገለጹት ዝቅተኛ ርቀቶች የበለጠ ወደ ተክሎች መቅረብ የለበትም፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| 7.1.1 | **ከ33ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ** | **2.5 ሜትር** |
| 7.1.2 | **ከ33ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ66ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ** | **6.0 ሜትር** |
| 7.1.3 | **ከ66ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ132ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ** | **13.0 ሜትር** |
| 7.1.4 | **ከ132ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ230ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ** | **15.0 ሜትር** |
| 7.1.5 | **ከ230ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ400ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ** | **19.0 ሜትር** |

7.2 **በማንኛውም ጊዜ ከምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመሩ ቀጥታ ወደላይ ያለው ቦታ ከተክሎች ነጻ መሆን አለበት፡፡**

## 8 ከሌሎች መስመሮች መጠበቅ ስለሚገባው ርቀት

8.1 **በማንኛውም ጊዜ ቢሆን እንደየሚመለከተው የመስመሩ ቮልቴጅ መጠን አንድ የምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመር ወደ አንድ የኮሙኒኬሽን መስመር ክፍል ቀጥሎ ከተገለጹት ዝቅተኛ ርቀቶች የበለጠ መቅረብ የለበትም፡፡**

| | | |
|---|---|---|
| 8.1.1 | **ከ1ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ** | **1.2 ሜትር** |
| 8.1.2 | **ከ1ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ33ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ** | **1.8 ሜትር** |
| 8.1.3 | **ከ33ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ132ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ** | **4.6 ሜትር** |
| 8.1.4 | **ከ132ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ230ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ** | **6 ሜትር** |
| 8.1.5 | **ከ230ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ400ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ** | **9 ሜትር** |

8.2 የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (8.1) ድንጋጌዎች በባለፋይበር ኦፕቲክ የኮሙኒኬሽን መስመሮች ላይ ተግባራዊ አይሆኑም::

8.3 በማንኛውም ጊዜ ቢሆን እንደየሚመለከተው የመስመሩ ቮልቴጅ መጠን አንድ የምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመር ወደ ሌላ የምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመር ቀጥሎ ከተገለጹት ዝቅተኛ ርቀቶች የበለጠ መቅረብ የለበትም::

8.3.1 ከ1ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ 0.6 ሜትር

8.3.2 ከ1ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ33ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ 1.2 ሜትር

8.3.3 ከ33ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ66ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ 4.0 ሜትር

8.3.4 ከ66ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ230ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ 4.5 ሜትር

8.3.5 ከ230ሺ.ቮ. በላይ ሆኖ ግን ከ400ሺ.ቮ. ያልበለጠ በሚሆንበት ጊዜ 7.0 ሜትር

8.4 የአንድ የምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመር የታችኛው ሰርኪት መደበኛ የቮልቴጅ መጠን ከላይኛው ሰርኪት መደበኛ የቮልቴጅ መጠን መብለጥ የለበትም::

## 9 ስለቮልቴጅ ሀርሞኒክ ዲስቶርሽን

9.1 ሀርሞኒክ የቮልቴጅ ዲስቶርሽን የአርኤምኤስ ቮልቴጁ ከመሠረታዊው አርኤምኤስ ጋር ሲነጻጸር የሚኖረውን መቶኛ የሚያመለክት ሆኖ ለዝቅተኛና መሀከለኛ የአቅርቦት ቮልቴጆች የእያንዳንዱ ሀርሞኒክ የቮልቴጅ ዲስቶርሽን መጠን ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ከፍተኛው መጠናቸው መብለጥ የለበትም::

9.1.1 ለ3ኛ ደረጃ ሀርሞኒክ 5 መቶኛ

9.1.2 ለ5ኛ ደረጃ ሀርሞኒክ 6 መቶኛ

9.1.3 ለ7ኛ ደረጃ ሀርሞኒክ 5 መቶኛ

9.1.4 ለ9ኛ ደረጃ ሀርሞኒክ 5 መቶኛ

9.1.5 ለ11ኛ ደረጃ ሀርሞኒክ 3.5 መቶኛ

9.1.6 ለ13ኛ ደረጃ ሀርሞኒክ 3 መቶኛ

9.2 አጠቃላይ የሀርሞኒክ ዲስቶርሽን መጠን ከ 8 መቶኛ መብለጥ የለበትም::

# ምዕራፍ ሦስት

# ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## 10 የምሰሶዎችና ታወሮች አተካከል

ምሰሶዎች፣ ታወሮችና ሌሎች የምድር በላይ የኤሌክትሪክ መስመር ተሸካሚዎች: :

10.1 በተቻለ መጠን ወደላይቀጥ ብለው የቆሙ መሆን አለባቸው::

10.2 ከመንገዱ ጠርዝ ወደመኪና መንገድ አቅጣጫ ቀጥ ብሎ ካለው አቋቋም ቢበዛ ከ5 ዲግሪ በላይ መዝመም የለባቸውም::

10.3 በሌሎች አካባቢዎች ቀጥ ብሎ ካለው አቋቋም ቢበዛ ከ10 ዲግሪ በላይ መዝመም የለባቸውም::

## 11 ስለኤሌክትሪክ መስመሮች አቀማመጥ፣ ሽፋንና ከአደጋ አጠባበቅ

11.1 ማንኛውም ከምድር በላይ ያለ የአንድ የኤሌክትሪክ መስመር ክፍል ከመሬት ጋር ካልተያያዘና ከህንጻዎች ወይም ግንባታዎች ላይ፣ ውስጥ፣ በስተጎን ወይም አጠገብ ከተተከለ ወይም ተደግፎ ከቆመ መወጣጫ፣ መሰላል ወይም ሌላ ዓይነት ግንባታ ላይ በመሆን በቀላሉ በእጅ የሚደረስበት ከሆነ:

11.1.1 የኤሌክትሪክ ኃይል እንዳያገኝ መደረግ አለበት፣ ወይም

11.1.2 ከሜካኒካል አደጋ ወይም ንክኪ በበቂ ሽፋን የተጠበቀ መሆን አለበት፣ ወይም

11.1.3 አደጋ እንዳያስከትል በቂ መከላከያ ሊደረግለት ይገባል::

11.2 *ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ሁኔታዎች ካልተሟሉ በስተቀር ይህ አንቀጽ ባለፈቃዱን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (11.1) ምክንያት ካልሆነ በስተቀር እንዲሸፈን ወይም ከአደጋ እንዲጠበቅ የማያስፈልገውን ከምድር በላይ ያለ የማንኛውንም የኤሌክትሪክ መስመር ማንኛ ውንም ክፍል እንዲሸፍን ወይም ከአደጋ እንዲጠብቅ አያስገድድም፡፡*

11.2.1 *መስመሩ በቀላሉ እንዲደረስበት ስላደረገው ህንጻ ወይም ግንባታ ሥራ በቂ ማስጠንቀቂያ ከተሠጠው፣ እና*

11.2.2 *በመሀከላቸው ሌላ ስምምነት ከሌለ በስተቀር መስመሩ በቀላሉ እንዲደረስበት በሚያደርገው ህንጻ ወይም ግንባታ ኃላፊ የሆነ ሰው መስመሩን ለመሸፈን የሚያስፈልገውን ተገቢ ወጪ ከከፈለው ወይም ሊከፍለው ከተስማማ፡፡*

11.3 *ይህ አንቀጽ ከዝቅተኛ ቮልት መስመር ውጪ ላለ ለማንኛውም መስመር ጊዜያዊ ሽፋን ማድረግን አይደነግግም፡፡*

## 12 *ቅጣት*

*የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው አግባ ባላቸው የአዋጁና የደንቡ ድንጋጌዎች መሠረት ይቀጣል፡፡*

## 13 *መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ*

*ይህ መመሪያ ከታህሣሥ 1 ቀን 1998 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡*

*አዲስ አበባ ህዳር 30 ቀን 1998 ዓ.ም*

*ጌታሁን ሞገስ*

*የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር*